Anthrax

Amharic



# አባ ሰንጋ (አንትራክስ)

## አባ ሰንጋ ምንድን ነው?

አባ ሰንጋ በረቂቅ ሕዋሳት ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። የአባ ሰንጋ በሽታ በተለያዩ መንገዶች የሚከሰት ሲሆን ለበሽታው የተጋለጠ ግለሰብ የተለያዩ የሕመም ስሜቶች ሊሰሙት ይችላል። ለምሳሌ ኃይለኛ የሆድ ሕመም (የተበከለ ምግብ ሲበላ እንደሚያሳምመው ዓይነት)፣ የቆዳ በሽታ እና የመሳሰሉት ናቸው። ሌላው የበሽታው ዓይነት (የእስትንፋስ አባ ሰንጋ) የሚመጣው ረቂቃን ነፍሳቱን ከአየር ጋር ወደ ውስጥ ሲተነፍሱት ነው። ምልክቶቹ የሚታዩት ለበሽታው ከተጋለጡ በኋላ እስከ ሰባት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ነው (ባብዛኛው ከሁለት እስከ አምስት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ነው)። ምልክቶቹ እንደ በሽታው ዓይነት ይለያያሉ፦



*የአባ ሰንጋ ረቂቃን ነፍሳት*

- **የቆዳ አባ ሰንጋ** ቆዳ ላይ የሚወጣ እብጠት ሆኖ ይጀምራል። ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ ውሃ ይቋጥራል ከዛም መሃከሉ ላይ ጥቁር የሆነ የማያም የቁላ ቁስል ይሆናል። ቁስሉ አካባቢ ያሉ እጢዎች ሊያብጡ ይችላሉ። የቆዳ አባ ሰንጋ በአንቲባዮቲክ በቀላሉ ሊታከም ይችላል።
- **የአንጀት አባ ሰንጋ** እምብዛም አይከሰትም። በማቅለሽለሽ፣ ምግብ አልበላ በማለት፣ በማስታወክና በትኩሳት ይጀምራል። እነዚህ ምልክቶች በሆድ ሕመም፣ ደም በማስታወክና በኃይለኛ ተቅማጥ ይከተላሉ። የአንጀት አባ ሰንጋ ካያዝዎት የአንቲባዮቲክ ሕክምና በቶሎ መጀመር አስፈላጊ ነው።
- **የእስትንፋስ አባ ሰንጋ** የሚጀምረው ጉንፋንን በሚመስሉ ምልክቶች ነው (ሳል፣ ትኩሳት፣ የጡንቻ ሕመም)። እነዚህ ምልክቶች ከሁለት እስከ ሶስት ቀን ከቆዩ በኋላ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን የጠፉ ይመስላሉ። ከዛም በሽታው ተመልሶ ኃይለኛ የሳንባ ችግሮች፣ የመተንፈስ ክብደትና ድንጋጤ ሊያስከትል ይችላል። ካልታከመ የእስትንፋስ አባ ሰንጋ በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል - ከመቶ ታማሚዎች ውስጥ እስከ 90 ይገድላል። በ2001 በደረሰው የአባ ሰንጋ በሽታ፣ ሕክምና ጋገኙት ውስጥ ሟቾቹ ከመቶ 40 ነበሩ።

## አባ ሰንጋ የሚይዘው እንዴት ነው?

የአባ ሰንጋ ረቂቅ ሕዋሳት ወደ ሰውነታችን ከመግባታቸው በፊት “ስፖር” የሚባል ደረቅ መከላከያ ሽፋን ያበጃሉ። በ”ስፖር” መልክ ሲሆን አባ ሰንጋን መግደል አስቸጋሪ ነው። “ስፖሮች” በተፈጥሮ አፈር ውስጥ ይገኛሉ - ለብዙ ዓመታትም መኖር ይችላሉ። እንደ ከብት፣ በግ፣ ፈረስና ፍየል የመሳሰሉ እንስሶች አፈር ውስጥ ካለ አባ ሰንጋ ጋር ከተነካኩ በሽታው ሊይዛቸው ይችላል።

የአባ ሰንጋ በሽታ በበሽታው ከተበከሉ እንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፈው በበሽታው የተበከለን እንስሳ በመመገብ ወይንም የእንስሳውን ውጤቶች በመንካት ነው። በተፈጥሮ የሚመጣ የሰው አባ ሰንጋ በሽታ በአሜሪካን አገር ውስጥ ያልተለመደ ነው።

እ.ኤ.አ. በ2001 ዓ.ም. በተከሰተው የአባ ሰንጋ በሽታ ሰዎች በበሽታው (በእስትንፋስና በቆዳ አባ ሰንጋ) የተለከፉት ሁን ተብሎ በበሽታው ሕዋስ የተመረዙ ፖስታዎችን በመንካት ነበር። ብዙ ሰዎች ባሉበት ቦታ ላይ ረቂቃን ነፍሳቱ በአየር ውስጥ ሊበተኑ ይችላል የሚል ሐሳብም አለ። ይህ ቢከሰት ውጤቱ ብዙ ሰው የእስትንፋስ አባ ሰንጋ ይዟቸው እንደሚታመሙ ነው።

## ከሌላ ሰው ሊይዝ ይችላል?

***አይችልም!*** ሊይዝ የምችለው “ስፖሮቹን” ወደ ውስጥ በመተንፈስ፣ የተበከለ ሥጋ በመብላት ወይም “ስፖሮች” ቆዳዎትን ከነኩ ብቻ ነው። አባ ሰንጋ የያዛቸው ሰዎች ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፉ አይችሉም።

## ለምንድነው የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል የሚባለው?

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

አባ ሰንጋ ከዚህ በፊት በኦክቶበር 2001 ዓ.ም. ላይ በ"ስፖሮች" የተበከለ ፖስታ በመጠቀም እንደ ሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ለማሠራጨት ተጠቅመውበታል። ሃያ ሁለት ሰዎች ተመርምረው አባ ሰንጋ ተገኝቶባቸው አምስት ሰዎች ደግሞ ሞተዋል።

ከዚህም በላይ እንደሚታወቀው አሜሪካን አገርና የቀድሞው ሶቪዬት ዩኒየን አባ ሰንጋን እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም ተመራምረውበታል። ሌሎች አገሮች አሁን ይህንን ሙከራ ቀጥለውበታል ተብሎ ይታመናል።

የ U.S. Centers for Disease Control and Prevention (CDC) የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያዎች ባሕርዮች ናቸው ብሎ ከሚተነትናቸው ውስጥ ብዙውን አባ ሰንጋ ይዞ ይጋኛል፦

- ከሰው ወደ ሰው ባይተላለፍም በቀላሉ ማዛመት ይቻላል።
- በሰው ጤንነት ላይ እስከ ብዙ ሞት የሚያስከትል ሰፊ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል።
- ሰፊ ሽብርና ማኅበራዊ ሁከት ሊፈጥር ይችላል።
- ለአባ ሰንጋ ጥቃት ለመዘጋጀት ልዩ ዓይነት እርምጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

## አባ ሰንጋ ሊታከም ይችላል?

ሁሉም ዓይነት አባ ሰንጋ በአንቲባዮቲክ ሊታከም ይችላል። ሕክምናን በአስቸኳይ መጀመር በጣም አስፈላጊ ነው። ለበሽታው የተጋለጡ ሰዎች በአስቸኳይ ሕክምናውን ከጀመሩ በሽታውን ማስቀረት ይቻላል።

## አባ ሰንጋ እንዳይዝ መከላከል ይቻላል?

ከመከላከያ መንገዶች ሁሉ የተሻለው ለበሽታው የተጋለጡ ሰዎች በቶሎ የአንቲባዮቲክ ሕክምና መጀመር ነው።

የጦር ኀይሎች የሚጠቀሙበት የአባ ሰንጋ ክትባትም አለ። መከላከያ ለመፍጠር ስድስት የመጀመሪያ ክትባቶችና ዓመታዊ ክትባት ያስፈልገዋል። ሆኖም ክትባቱ በትንሹ ሲሆን የሚገኘው ሲቪሊያን ዶክተሮች ሊያገኙት አይችሉም። እንደማንኛዉ ክትባት አንዳንዴ አስጊ ሊሆን ይችላል። ጥቃት ቢኖር የት ወይም መቼ የተወሰነው ክትባት እንደሚያስፈልግም አይታወቅም። በነዚህ ምክንያቶች ለሰፊ ሕዝቡ በአሁኑ ጊዜ ክትባት ያስፈልጋል ተብሎ አይታሰብም።

## ለድንገቱ አንቲባዮቲክ ባስቀምጥ ጥሩ ነው?

***አይደለም!*** አንቲባዮቲክ ለራስ መስጠት ጎጂ ሊሆን ይችላል። በተለይ ለነፍሰጡር ሴቶች፣ ለልጆችና የአንቲባዮቲክ አለርጂ ላለባቸው ሰዎች አንቲባዮቲክ መውሰድ አደገኛ ሳይዲፌክት ሊኖረው ይችላል። አንቲባዮቲክ በብዛት መውሰድም በአንቲባዮቲክ ሊታከሙ የማይችሉ ኃይለኛ ነፍሳቶች ሊፈጥር ይችላል።

የሕዝብ የጤና ጥበቃ ድርጅቶች፣ ሆስፒታሎችና ባጠቃላይ በሚኔሶታ የሚገኙ ክሊኒኮች በሽታ የሚፈጥር ምንም ዓይነት አላግባብ እንቅስቃሴ እንዳይኖር ነቅተው ይጠብቃሉ - የአባ ሰንጋንም ጥቃት ጨምሮ። የአባ ሰንጋ ጥቃት ቢታይ የሚኔሶታ የጤና ክፍልና የአካባቢው የጤና ክፍሎች በፍጥነት እርምጃ ይወስዳሉ። ለበሽታው የተጋለጡ ሰዎችን ለማወቅ አስፈላጊውን እርምጃ ወስደው አንቲባዮቲክ መውሰዳቸውን ያረጋግጣሉ።

## ለአባ ሰንጋ ወይም ለአባ ሰንጋ ለተጋለጡ ሰዎች የሚሰጥ ቴስት አለ?

የእስትንፋስ አባ ሰንጋ ባብዛኛው የሚታወቀው ደም ውስጥ የአባ ሰንጋን ረቂቃን ነፍሳት በመፈለግ ወይም ከሳንባና ከመተንፈሻ ቱቦዎች ፋሳሽ በመውሰድ ነው። የቆዳ አባ ሰንጋ የሚመረመረው ቆዳን በመፈተሽ ወይም በማየት ነው።

***ለአባ ሰንጋ መጋለጥዎን ለማወቅ መውሰድ የሚቻል ምንም ዓይነት ቴስት የለም።***

## ለአባ ሰንጋ የተጋለጥኩ ከመሰለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ጥርጣሬ የሚያሳድር እንቅስቃሴ ካዩ በአካባቢዎ ለሚገኘው የሕግ አስከባሪ ድርጅት ያሳውቁ። ለአባ ሰንጋ መጋለጥዎን ማረጋገጥ የሚቻልበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም። ተጋልጫለሁ ብለው የሚያምኑ ከሆነ ግን ወይም ማንኛውም ዓይነት ሌላ የጤና ችግር ካለብዎት ዶክተርዎን ያነጋግሩ። ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ካለብዎት ወይም ስለሽብር ጥቃት ጭንቀት ካለብዎት የአእምሮ ጤንነት ባለሞያ ለማነጋገር ይሞክሩ።